# ወደ ራሴ ስመለከት፡- እንደ እኔ ላለ ዲሞክራሲ፣ ነጻነትና አገር አይገባውም

ብዙ ተቺዎች ወይም ሃያሲዎች ወቃሾችና ከሳሾች ባሉበት አገር ታታሪና ትጉህ ሰራተኞች ጥቂት ናቸው። ጣት መጠንቆል ቀርቶ ወደራስ መመልከት ተገቢ የሆነበት ደረጃ ላይ በመድረሳችን ሌሎች ምን ሰሩ ሳይሆን እኔ ምን ስለሰራሁ ነው ፍትህ፣ ነጻነት አገርና ዲሞክራሲ ይገባኛል ማለት የምችለው? የሚለው ጥያቄ በነፍስ ወከፍ መመለስ ያለበት ይመስለኛል። ይህ ጥያቄ አሁን ለሚደርስብን በደልና ለትውልድ ለምናቆየውም ጥፋት መልስ ሰጪ ነውና አመልካች ጣታችንን ለጊዜው ረስተን ወደ ራሳችን የሚጠቁሙትን አብላጫ ጣቶች ጥያቄ መልስ እንስጥ። ብዙዎቻችን አሁን ባለንበት እንቀጥል የምንል ከሆነ በድምጽ ብልጫ ሽንፈትን ተቀብለናል ማለት ነው። እኔ በበኩሌ እንዲህ እራሴን አየሁ። እናም መለወጥ እንዳለብኝ አመንኩ። እናንተስ?

በመጀመርያ እኔ አገር አልባ፣ ለትግል ዘወር ካሉት ጋር የማልቆጠር አገሬን ለጠላት ትቼ ነብሴን ለማዳን ወይንም ኑሮዬን ለማሸነፍ የፈረጠጥኩ ፈሪ ሰው ነኝ። ቆሜ መሞገት ያልቻልኩ ወይም ተጨቆንኩ ከሚለው አእላፍ ወገኔ ጋር መተባበር ማስተባበርና ፈሪውን ጠላቴን ማሸነፍ ያልቻልኩ ደካማ ሰው ነኝ። ስሜም ላይ ቅጽል ገብቶለታል። **ስደተኛ** የሚል። የሚሰደድ ባለበት መኖር የማይችል ነው። ታድያ ስደት መብቴ ይመስል የተሰደድኩባቸውን አገሮች ሳማርር ለጉድ ነው። የሚሉኝን ስለማላውቅ ባውቅም ጆሮ ዳባ ልበስ ስለምል እንጂ በድህነቴ የሚሳቅብኝ፣ አብሮ ለመብላት እንጂ አብሮ ለመስራት የማይችሉ ለመበተን የፈቀዱ ሕዝቦች እንደሚሉኝ ብቀበል ደግ ነበር።

ይህን ባውቅም ግን እኔ ራሴን ከጥሩዎች መድቤ ሌሎቹ ሁሉ መጥፎ በመሆናቸው ነው እያልኩኝ ስደትን እንደ ማዕረግ ይዤ ወንድም እቶቼን ለስደት እጋብዛለሁ። ከአገሬ ጋር ያለኝ ቁርኝት ወደ ትዝታነት ከዞረ እኮ ያለቀ ነገር ነው። አገሬ የምትታሰበኝ እናት አባቶቼ እስካሉ ድረስ ወንድም እህቶቼ እስካሉ ድረስ ብቻ ከሆነ ቁርኝቴ የላላ ነው። አገሬን የምናፍቃት ልፈነጭባት፣ ከሰው በልጬ ልታይባት ከሆነ የስነልቡና ችግር ያለብኝ ሰው ነኝ ማለት ነው። የተሰራሁበት አፈርና ውሀ፣ ያነጸኝ ሕዝብና ባህል፣ ያኮራኝ ታሪክና ቅርስ በደምና ስጋዬ ውስጥ ከሌሉና በሄድኩበት የምለምድ ከሆነ ግጦሽ በተገኘበት የምሰፍር ዐለም አቀፍ ዘላን እንጂ በሕዝብ የተከለለ በመልከዐምድር የተከተረ ሀገር  ባለሀብት አይደለሁም። ከነበርኩበትም ካለሁበትም ጠንካራ ቁርኝት ከሌለኝ በታሰርኩበት የገመድ እርዝማኔ ለእለት ጉርሴ መንቀሳቀስ እንጂ የኔ የምለው አገር እንዲኖረኝ የምተጋ አይደለሁምና ለወገኔ ዲሞክራሲና ነጻነትስ ምን ገዶኝ?

የኔ ነገር ለጉድ ነው። አገር ስትፈርስ ቆሜ ዝርዝር አወጣለሁ። እንዲህ አደረጉ እንዲህም አደረጉ እንዲህ ደግሞ ሊያደርጉ ነው እያልኩ ስዘግብ የስታቲስቲክስ ጽህፈት ቤት የቀጠረኝ ባለሞያ እንጂ ሀገሩን የተነጠቀ ባለሀገር አልመስልም። በቀደም ንጹሀን ሰዎችን ገደሉ፣ ትናንት ሕጻናትን አረዱ ስል የጠላቶቼን ጀብዱ እኔ የማወራላቸው እመስላለሁ። በእኔ ቢጤ የተሞላ ሁነኛ ሰው ያነሰበት መሬት ደግሞ ከሰፌድ ላይ እንደሚንገዋለል ብጣሪ እኔን ከድንበር ባሻገር በትነው አገሬን ገዢዎቼ ይሸጣሉ።

እንዲያ እያለ እንደ 'Osmosis' የተፈጥሮ ህግ አገሪቱ እንዳለች ሆና ባለሀገሮቹ ሌሎች ይሆናሉ። ይህን በዐይኔ በብረቱ እያየሁ  በቃ ብዬ በደልን ለማስቆም የራሴን ድርሻ ለማበርከት ሀሞት የለኝም። እኛ እናስጥልህ የሚሉኝን አላምናቸውምም፣ አልደግፋቸውምም። ነገር ግን ሰዉ ደሙን አፍስሶ አጥንቱን ከስክሶ ባቆመው ሀገር ውስጥ በድንግዝግዝ ፋይል ገብቼ በእርጥባን እየኖርኩ ድሎትንም እየተመኘሁ "ከእንግዲህ ይህ ዐለም ፍጹም ቤቴ አይደለም" እያልኩ እግዜርንም እዋሻለሁ። አገሬንም አሻሽጬ በገነት ለምሰራው ቤቴ 'ኢንቨስት' አደርጋለሁ። ታድያ ለእኔ አገር፣ ዲሞክራሲና ነጻነት እንደምን ይገቡኛል?

በቀደም እለት ስለሀገር ስናወራ ስንቱን ጉድ ስናዝረጠርጠው አመሸን። መተባበር እንደሚያስፈልግ ድጋፍ መስጠት እንደሚያሻ ተነጋገርን። የገረመኝ የአንደበታችን ስለት፣ የሀሳባችን ስምምነት ነበር። በስተመጨረሻ አንዱ ጉድ አደረገን። እስቲ ማውራት መልካም ነው መስራት ደግሞ ድንቅ ነገር ነው እያለ ከሁዋላ ኪሱ ቦርሳ ውስጥ በትልቁ 100 የተጻፈበት ኖት አወጣና እስቲ የኢትዮጵያ ጉዳይ ግዴ ነው ለሚል ለአንዱ ድጋፍ እንስጥ አለ። ጥሩ ሀሳብ መልካም ጅምር እያልኩ እጄን በየአቅጣጫው ብልከው ቦርሳዬ ለምን አይጠፋብኝም። እጄ ለዚህ ሲሆን ይደናገረዋል መሰለኝ ወዲህ ብዳብስ ወዲያ ብዳብስ ኪሴ ውስጥ ያሉትን ኖቶችም እጄ አይመዛቸውም። ለካስ ብዙዎቹ እንደ እኔው ናቸው። ሲያወሩ ነው የሚመቻቸው።

አንደኛው ሀሳቡ ሸጋ እንደሆነ ገልጾ ከትናንት ወዲያ ለታማሚ እናቱ ያለችውን ጠራርጎ ባይልክ ኖሮ ብዙ ገንዘብ ለዚህ ቅዱስ ሀሳብ ይሰጥ እንደነበረ አስተዛዝኖ ነገረን።  ይህ ብቻ ሳይሆን አገር ቤት ስለአለው ሕክምና መጥፎነት ግማሽ ሰዐት አወራልን። ሌላኛው ለሰርግ የነበረበትን ወጪ ዘርዝሮ ዘርዝሮ ሲነግረን ምነው እንዲህ ያለ አሳብ ውስጥ ከሚገባ ባላገባ ኖሮ እስከንል ድረስ ቅቤ በጠጣ ክትፎ እያወራረደ ችግሩን ነገረን። ሌሎቻችን በወይን እያጣጣምን ሰማነው።

ቁምነገር በበር ሲገባ ተግባር በመስኮት ሹልክ አለ።  በመጨረሻም በመጣልኝ ሀሳብ ፋይሉ ተዘጋ። እንዲያው ለስማችንም እንዲሆን በደንብ አስበንበት አለ አይደለም በደንብ ተዘጋጅተንበት በቅርቡ አንድ ነገር እናድርግ ስል ሁሉም ተመችቶአቸው በፈገግታ በሞቅታ ሀሳቤን ተቀበሉት። ሁሉም የእፎይታ ይመስል መለኪያ ውስጥ ያላቸውን መጠጥ በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ አደረጉ። ምክንያቱም ይቺ ነገር

የማርገቢያ ዘዴ መሆንዋን ሁላችንም እናውቃለና። ከዚህ ቀደም ስንቱን ብለን የውሀ ሽታ ሆኖ ቀርቶአላ! እናም ከደርዘን ሰዎች መካከል ወጥታ የነበረችው አንድ መቶ እንደ አወጣጥዋ ተመልሳ መግባት ተገደደች።

በምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፣ ሀምሳ ሎሚ የተሸከመ ሰው ባይ ላግዝህ ከምለው ይልቅ በእጁ ከሚያንጠለጥለው በአናቱ ላይ ቢሸከመው ይቀለው ነበር። ወይም መሸከሙ ካልቀረ ለምን መቶ አያደርገውም እያልኩ መከራከርን እመርጣለሁ እንጂ እስቲ ላግዝህ? ምን ሲደረግ? የሚገርመው ምላሴ የወቀሳ ብራቁን፣ የትችት መድፉን፣ የመፍትሄ ሀሳቡን ያንጣጣዋል። እናም እኔ መፍትሄ ጠቋሚ ነኝ፣ እኔ የተሳሳቱትን አራሚ ነኝ። በተገኘው መድረክ ሁሉ ወግ የምጠርቅ ከስራው ቦታ ለመገኘት ግን ያልቻልኩ የመፍትሄው አካል የመሆን አቅም ያነሰኝ ልፍስፍስ ያልኩ ፍጡር ነኝ በቃ!! ተግተው የአቅማቸውን እንሥራ የሚሉትም ለኔ ወቀሳና ክስ መልስ ሲያዘጋጁ ጊዜው ይባክናል።

እንዲያው የሚገርመኝ አንድ ሰው ቢላ ይዞ አንገቴን መገዝገዝ ቢጀምር ቻይና እንዲህ ያለ ቢላ ባታመርት ኖሮ ስቃዬ አይበዛም ነበር እል እንደሆን እንጂ ለመንፈራገጥ እንኳ መሞከሬን እንጃ። ምክንያት መፈለግ ለምዶብኛላ። ይህ እውነት ባይሆን ወያኔ እንዲህ ባላፈዘብኝ ነበር። ታድያ ለኔ ለተሸናፊው ዲሞክራሲ፣ ነጻነትና  አገር ስለምን ሊኖረኝ ይገባል? በማን መስዋዕትነት? በማን ትግል? በማን ደም? በነሸብሬ? በጨቅላዎቹ? በነብርቱ በነቴዲ ነው ወይስ በአረጋውያኑ? ሽብር ተመችቶኝ፣ ስድብ አበረታቶኝ፣ ውርደት ማዕረግ ሆኖልኝ ሳላፍር፣ ሳልሸማቀቅ፣ ሳልቆጣና በቃ! ሳልል የባሰ አታምጣ እያልኩ የሸክም ጫንቃዬን እያደነደንኩ የምኖር ከሆነ፣ ለእኔና እንደ እኔ ላሉቱ ነጻነት፣ ፍትኀ፣ ዲሞክራሲና አገር ሊኖረን እንዴት ይቻለዋል?

አሁን እንዲያው ወያኔ ኢትዮጵያን ቢሸረካክታት፣ ቢቀረዳድዳት ማን ከልክሎት? ቢሻው ለቻይና ቢሸጣት፣ ለአረብ ቢመጸውታት ወይ ለሕንድ ቢቸረችራት ከቢጤዎቹ ጋር ሰብስብ ብለን  ዋጋው አነሰ በዛ እያልኩ ከማውራትና ማን ቢገዛ ይሻል እንደነበር ከማስረዳት እልፍ እል ይሆን? እንኳን አገሬን እኔን እራሴን ታላቅ ቅናሽ የሚል ለጥፎብኝ ቢሸጠኝ ገዢ ፍለጋ እቁለጨለጭ እንደሁ እንጂ ሌላ ማድረግ የምችል አይመስለኝም። ከአደጋ በእጅጉ እርቄ በነጻነት እየኖርኩ ነጻነት ለተጠሙ ወገኖቼ ምንም ማድረግ ከተሳነኝ ለጥፋት ፈርጀባቸዋለሁ ወይም አንድ የጎደለኝ ነገር አለ። አይመስላችሁም? ታድያ እንደ እኔ ላለ ዲሞክራሲ፣ ነጻነት ብሎም አገር ስለምን ይገቡኛል?

ዳኛቸው ቢያድግልኝ
biyadegelgne@hotmail.com